# ምዕራፍ ሦስት

## ተዝካርና ፍትሐት

መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን በመጽሐፈ መክብብ በምዕራፍ ፫ በቁጥር ፳ ላይ «ሁሉ ወደ አንድ ቦታ ይሄዳል ሁሉ ከአፈር ነው ሁሉም ወደ አፈር ይመለሳል» እንዳለው ሁሉ በቀዳሚው አዳም ትዕዛዝ መጣስ ምክንያት ባጠቃላይ በአዳም ዘሮች ላይ የሞት አዋጅ ታውጇል ።

ዛሬ እገሌ ወእገሌ ሳይል ሁሉንም በጊዜው የሚያስተናግደው መልአከ ሞት ያልገባበት ቤት ያልነካው ሰው እንደሌለ አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው እሙን ነገር ነው። ሞት በእያንዳንዱ ሰው ጫንቃ ላይ ተሰይሞ ያለ ነው ። ይህ ሞት አንጀቱን ያላሳረረው ፤ በቀቢጸ ተስፋ ባሕር ያላሰጠመውና ቅስሙን ያልሰበረው ሰው ቢኖር ዓለምን ንቆ እንደ መርገም ጨርቅ ተጠይፎ ለወንጌል ያደረ የወንጌል አርበኛ ነው ። አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ግን ልቡ በሞት የደማ የሞት ባላንጣ ነው ።

የቴክኖሎጂው ርቀትና ምጥቀት የሞትን መውጊያ ሊያስወግድ አልቻለም ዛሬ በዓለማችን ላይ አሳዛኝ የሆኑ አሟሟቶች ይከሰታሉ ።

በጣም የሚፋቀሩ ባልና ሚስት በሞት ምክንያት ይለያያሉ እናት የምትወደው ልጅዋን በሞት ተነጥቃ አንጀትዋ ስፍስፍ እስኪል ታለቅሳለች ። ግን መፍትሔ አይኖረውም ። እንደ ነፍሱ አድርጎ የሚወዳት የትዳር ጓደኛው የሞተችበት ሰው ሚስቱን ዳግመኛ ሊያገኛት ስለማይችል ለሟች ሚስቱ የአበባ ዝንጣፊ በመውሰድ በሐውልትዋ ላይ በማስቀመጥ ሟች ፍቅረኛውን ያዘክራል ። ይህ ዓይነቱ ሙታንን የማዘከር ልምድ በነጮች ዘንድ የተለመደ ከሆነ ውሎ ከርሟል ።

በአንጻሩ ደግሞ በሞቱ ወገኖቻቸው ሐውልት ላይ ወቅት እየጠበቁ በመሔድ ምርር ያለ ለቅሶ የሚያለቅሱና ራሳቸውን ለልክፍት አሳልፈው የሚሰጡ ሰዎች ቁጥርም ጥቂት አይደለም ።



እነዚህ ሁሉ ግን ለሟቹ የሚሰጡት ጥቅም አንዳችም የለም ። በምውታን ሐውልት ላይ አበባ የማስቀመጡ ልምድ ምናልባት ቋሚውን ሊያስደስትና ሊያረካ ቢችልም ሟችዋ ግን የመጣላትን (አበባ መዓዛ በአፍንጫዋ ስባ ትፍሥሕት ልብ የሚሰጣት ሆኖ አይደለም ። አድራጊዎቹም ይኸን አበጥረው አንጠርጥረው የሚያውቁት እውነታ ነው ። ዳሩ ግን የማይጎዳ ባሕል ስለሆነ በነጮች ዘንድ የማይቀር ልምድ ሆኖ ተይዞአል ።

በእኛ ቤተ ክርስቲያን ባህል ደግሞ ከዚህ ለየት ያለ የሙታን መታሰቢያ ይደረጋል ። ምናልባት እነሱነታቸውን የዘነጉና ፈረንጅኛውን ብቻ የሚያደንቁ አንዳንዶች ይህን ጥንተ መሠረቱ ከአበው ሲያያዝ የመጣውን ሐዋርያዊ ሥርዓት ሲንቁና ሲተቹ ይታያሉ ። ይኸውም ቤተ ክርስቲያን ለሞቱ ወገኖችዋ የምታደርገው ጸሎተ ፍትሐትና ተዝካር ነው ። ዛሬ ምእመናን ለሞቱ አማንያን ወገኖቻቸው የሚያደርጉት ጸሎተ ፍትሐትና ተዝካር አውሮፓውያን በሞቱ ሰዎች ሐውልት ላይ ከሚያስቀምጡት የአበባ ዝንጣፊ አንሶና ተንውሮ እንደ መጥፎ ልምድ ተቆጥሮ በአንዳንድ አላዋቂዎች ዘንድ ሲተች ይሰማል ።

ግን ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት እንደመሆንዋ ሁሉ እምነትዋና ሥርዓትዋ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ።

በእያንዳንዳችን ሊጤን የሚገባው ዓቢይ እውነት አለ ይኸውም የፍጡር በደለኝነትና የእግዚአብሔር ቸርነት ። የእግዚአብሔር ርህራሄውና ቸርነቱ ወሰን የለውም ። ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስ እንደተናገረው «ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው ርኅራሄው አያልቅምና» ሰቆቃው ኤርምያስ ፫.ቁ. ፳፪

በእርግጥም ነው ከሰው ልጅ ጥፋት ይልቅ የእግዚአብሔር ምሕረት እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደ ምድር አሸዋ የበዛ ነው ። የዝናምን ጠብታ የቆጠረ አለ? እንደዚያው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቸርነት ልንወስነው አንችልም ። ለዚህም ማረጋገጫ ዛሬ ዓለም በከፍተኛ የኃጢአት ደረጃ ላይ ሳለ ፈጥኖ በመቅሰፍት አለመጥፋቱ ነው ። ምክንያቱም ኃጢአት በሚበዛበት ቦታ የእግዚአብሔር ቸርነት ይበዛልና ። ክርስቲያኖች የአምላክን ቸርነትና ርህራሄ ያውቃሉ ይመሰክራሉ ። ይህ ያልገባቸውና ያልተዋጠላቸው ከእግዚአብሔር ቸርነትና ርህራሄ ውጭ



www.ethiopianorthodox.org

የሆኑ አንዳንዶች በእግዚአብሔር ቸርነት ጥላ ሥር የተጠለሉትን አማንያን ልቡና ለማጠራጠር በከንቱ እየደከሙ ነው ።

ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ይቅር ባይነት ወሰን የሌለው መሆኑን ስለምታምን ምንጊዜም ቢሆን ሰዎች ተስፋ እንዳይቆርጡ ታስተምራለች ከዚህ እምነትዋ በመነሣትም የበላይ ጠባቂዋ የሆነውን የመሲህ ክርስቶስን ትምህርት መሠረት በማድረግ በሃይማኖታቸው ጸንተው ለሞቱ ምዕመኖችዋ ጸሎተ ፍትሐት ተዝካር እንዲደረግ ታዛለች ።

ምናልባት ሰው ሊጸድቅ የሚችለው በሕይወተ ሥጋ ሳለ በሠራው የጽድቅ ሥራ ብቻ እንጂ ከሞተ በኋላ በሌሎች በሚቀርብለት መሥዋዕትና ጸሎት አይደለም የሚል ጥርጥር ያለበት ሰው ቢኖር የእግዚአብሔርን ቸርነትና ማዳኑን የካደ መሆኑን ሊያውቅ ይገባዋል ። ምክንያቱም የሌሎች ጸሎትና የእግዚአብሔር ቸርነት ሳይሆን የሰውየው ፍጹምነት ብቻ ለጽድቅ እንደሚያበቃ አድርጎ መወሰዱ ነውና ። ዳሩ ግን እንኳን የሰው ልጅ ሰማያት እንኳን በእግዚአብሔር ፊት ንጹሐን አለመሆናቸው በቅዱስ መጽሐፍ ላይ የተገለጸ ነው/ ፤

እንግዲህ ሰው ለመንግሥተ ሰማይ የሚበቃው በፍጹም ምግባሩ ሳይሆን በእግዘ አብሔር ቸርነት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ። ይህ ማለት ግን ምግባር አያሻም ማለት አለመሆኑ ግልጽ ሊሆን ይገባል ። ምግባራችን መንግሥተ ሰማያን እንድንወርስ ፍጹም አያደርገንም የእግዚአብሔር ቸርነት ካልታከለበት ለማለት ተፈልጎ ነው ። «ሰው ሆኖ የማይበድል እንጨት ሆኖ የማይጨስ የለምና ።

ምንም እንኳን ንስሐ የበደለን እንዳልበደለ የምታደርግ ደገኛ ሥርዓት ብትሆንም ምን ያህሉ ሰው ነው ለኃጢአቱ ሁሉ ንስሐ የሚገባው ። በዚህም አልን በዚያ ፈቃደ ሥጋ የሰለጠነበትን ሰው በሥራው ፍጹም ይሆናል ብሎ መገመት ስህተት ነው ። በእርግጥ ከማንኛውም ሰው ዘንድ ነቅ የሌለባት ፍጽምት ሃይማኖት ትኖረው ዘንድ ይጠበቃል በሃይማኖታችን ጥርጣሬ ሊኖርብን አይገባምና በእርግጥ በምግባርም እንደሰማዩ አባታችን ንጹሐን እንድንሆን ብንታዘዝም የባህርያችን ድክመት ፍጹማን ሊያደርገን አልቻለም በእሱ ቸርነት ፍጹምነት ደረጃ ላይ የደረሱ የሉም ማለት አይደለም ሰው ግን ምንም እንኳን የፍጹምነት ሥራ የሠራ ቢመስለውም ራሱን ፍጹም አድርጎ ማቅረብ



አይገባውም ። ለዚህም ምሳሌ ቅዱሳን ከበቁ በኋላ ራሳቸውን ኃጢአተኛ አድርገው ስለሚያቀርቡ «ኃጢአታችንን ይቅር በለን» ሲሉ ይጸልያሉ ።

ማንም ሰው በምሠራው ፍጹም ምግባር ለመንግሥተ ሰማይ እበቃለሁ ቢል በዚህ ሰው ልቡና ውስጥ ዲያብሎስ እግሩን አንፈራጦ መቀመጡን ልንገነዘብ ይገባል ። እንዲህ አይነት የትዕቢት አስተሳሰብ ከጥንተ ጠላት ዲያብሎስ የተገኘ ነውና ።

የአንድ ባህታዊ ታሪክ ለምሳሌነት እዚህ ላይ ሊጠቀስ ይችላል ከሰው ርቆ ንጽህ ጠብቆ ዳዋ ጥሶ ጤዛ ለብሶ ድንጋይ ተንተርሶ ድምጸ አራዊትን ጸብአጋንንትን ታግሶ ለብዙ ዘመን በብህትውና ይኖር ነበር ። ታዲያ ጌታ ተገልጾ «እንደ ሥራህ ልስጥህ እንደ ቸርነቴ» ቢለው ባሕታዊው በሥራው ተመክቶ «ቸርነትህንማ በከተማ የላመ የጣመ እየበሉ በፋሚሊ አልጋ ለሚንፈላሰሱ ምእመናን አድርገው ለእኔ ግን እንደ ሥራዬ ሥጠኝ ብሎታል»

በእርግጥ በሰው ሰውኛው አመለካከት ይህ ሰው በጾም በጸሎት በሰጊድ የተጠመደ ስለሆነ ሥራው ፍጹም ነውና ሥራው ለጽድቅ ያበቃዋል ልንል እንችል ይሆናል ። ዳሩ ግን ትሑቱ አምላክ ሳይቆጣ «እሺ እንዳልክ የሥራህን ዋጋ እሰጥሀለሁ» ነው ያለው ። የሥራው ውጤት ምን ሆነ? ከብህትውናው ወጥቶ ለብዙ ዘመን በእግዚአብሔር ጥበቃ ከኃጢአት ርቆ የነበረው ሰው በኃጢአት ማጥ ወድቆአል ።

ከዚህ የምንረዳው ቢኖር ሰው በሚሠራው ሥራ ብቻ ፍጹምና ለመንግሥተ ሰማይ የቢቃ ሊሆን አይችልም የእግዚአብሔር ቸርነት ሊታከልበት ይገባል ለማለት ነው ። ከዚህ በመነሳት ለሞቱ ክርስቲያኖች የሚደረገው ፍትሐትና ተዝካር አግባባዊ መሆኑን የመጽሐፍ ቅዱሳን ምሥክርነት በመጥቀስ መናገር እንችላለን ።

የእውነት አባት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረው ቃል አለ ይኸውም «ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ» የሚለው ነው ። ዮሐ. ወን. ፲፬. ቁ. ፲፬ ። በመሠረቱ ይህ አባባል ግልጽና የማያከራክር ሲሆን ቤት ክርስቲያናችንም ይህን አምላካዊ ቃል መሠረት አድርጋ ለሞቱ ምእመናን ጸሎተ ፍትሐት ብታደርግ የሚያስነቅፋት ሳይሆን የአምላክዋን ቃል በፍጹም



www.ethiopianorthodox.org

እምና ተግባራዊ በማድረግዋ የሚያስመሰግናት ነው ። የሚነቅፍ የሚጠራጠር እንጂ ያረጋገጠ አይደለምና ። የአምላካችን ቃል የታመነና ተፈጻሚነት ያለው ነው ለዚህም «የተናገርኩት ቃል ከሚያልፍ ሰማይና ምድር ቢያልፉ ይቀላል» ብሎ የተናገረው ሁሉ ተፈጻሚ እንደሚሆን አረጋግጦልናል ማቴ. ፳፬. ቁ. ፴፭

እንግዲህ በስሜ የምትለምኑትን ማናቸውንም ነገር አደርገዋለሁ እያለ ። አንዳንድ ተጠራጣሪዎች አማኞች በእምነት ስለሞተው አማኝ ወገናቸው የሚያቀርቡትን ልመና ዋጋ ቢስ አድርገው የሚያቀርቡት ከመጽሐፍ ቅዱስ ወጥተው በራሳቸው ሐሳብ ተመርተው መሆናቸውን ሊገነዘቡ ይገባል ።

ማንኛውም ክርስቲያን በፈጣሪው ቃል ላይ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታክል ጥርጥር ሊኖረው አይገባም «የሚጠራጠር ሰው የባህርን ማዕበል ይመስላል ለዚህ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች ነገር አይደረግለትም» እንደተባለ ሁሉ ለሚጠራጠሩ ለእነርሱ ባይሆን ለምናምን ለእኛ ግን እንደ እምነታችን ይሆንልናል ።

ሐዋርያት በሲኖዶስ ስለሞቱ ሰዎች ነፍስ ከገንዘባቸው ለድሆች ለጦም አዳሪዎች ይሰጸው ቱላቸው እንዲህም አድርጉ ብለን የምናዘው በሃይማኖት ጸንተው ለሞቱ ሰዎች ነው እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ መሲሕ ክርስቶስን ለሚክዱ (ለካዱ) ሰዎችስ በዓለም ያለውን ገንዘብ ኹሉ ቢመጸወቱላቸው ምንም አይጠቅማቸውም ብለዋል ።

ይህን ጌታ ራሱ ተናግሮታል «በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በደሉ ይቅር ይባልለታል በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ኹሉ ግን በዚህ ዓለምም ኾነ በሚመጣው በደሉ ይቅር አይባልለትም» ማቴ. ፲፪. ቁ. ፴፪ ።

በዚህ ዓለም የሚለው በሕይወተ ሥጋ እያለ ማለት ሲሆን በወዲያኛው ዓለም ሲል ደግሞ በአጸደ ነፍስ ያለውን ማንሳቱ ነው ።እንግዲህ በአጸደ ነፍስ ንስሐ ኖሮ አይደለም ዳሩ ግን በምድር ላይ ያሉ ወገኖቹ በሚያቀርቡለት ጸሎተ ፍትሐትና ተዝካር መማሩንና አለመማሩን ሲገልጽ ነው ። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስንና ጌታችን ክርስቶስን ፍጡር ያላለ የባህርይ አምላክነቱን የማነ የቤት ክርስቲያን አባል ከሆነ የሚደረግለት ጸሎተ ፍትሐት እንደሚጠቅመው መግለጹ መሆኑን ሁላችንም ልብ ልንል ይገባል ።



በሃይማኖት የሚመሥሉን ወገኖቻችን ሲሞቱ በሠሩት ኃጢአት ሞተ ነፍስ ተፈርዶባቸው ሲያል እንዳይገቡ መንግሥተ ሰማይ እንዲገቡ ብንጸልይ አንድም ፍቅርን ያመለክታል ከዚህም በተጨማሪ በወንጌል ቃል ላይ ያለንን ጽኑ እምነት ይገልጻል ።

በወንጌል ላይ እንደተዘ፡በው ጌታችን በዚህች ምድር ላይ በሥጋ ተገልጦ በሚመላለስበት ወቅት የእምነት ገመድ ስቦ ያመጣቸው ብዙ ሰዎች የሞቱ ወገኖቻቸውን እንዲያስነሳላቸው ያለምንም ጥርጥር ለምነውት ወገኖቻቸውን ከሞተ ሥጋ አድነዋል እንግዲህ ክርስቶስ ከሞተ ሥጋ ብቻ ሳይሆን ከሞተ ነፍስም ማዳን የሚችል የባህርይ አምላክ መሆኑን የሚያምን ሰው ሁሉ በፍጹም እምነት በሞት ለተለዩት ወገኖቹ በሠሩት ኃጢአት እንዳይፈረድባቸውና ከሞተ ነፍስ እንዲድኑ ቢለምን በእምነት ያቀረበው ጸሎት በጌታ ዘንድ ተቀባይነት አለው ጌታ አያደላምና ፡

ነገር ግን ጌታን ፈጽመው ለካዱ ቋንጃ ሲቆርጡ ደም ሲያፈሱ ለነበሩ አረመኔዎች ማርልን ብለን ጌታን የምንጨቀጭቅ አይደለንም ከላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ ይቅር የማይባል ኃጢአት አለና ዮሐንስም በመልእክቱ እንደገለጸው «ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባውን ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይለምን ሞትም የማይገባውን ኃጢአት ላደረጉት ሕይወት ይሰጥለታል ። ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ ስለ ዚያ እንዲጠይቅ አልልም አመፃ ሁሉ ኃጢአት ነው ሞትም የማይገባው ኃጢአት አለ» 1ኛ ዮሐንስ መል ፭ ቁ. ፲፮—፲፯ ።

ቤተ ክርስቲያንም ይህን አምላካዊ ቃል መሠረት አድርጋ ሃይማኖታቸውን ከደው ምግባር ትሩፋት አያስፈልግም ብለው አውቀው በኃጢአት ባህር ሲዋኙ ለኖሩ ሰዎች ቢሞቱ ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግ አትፈቅድም ። ዳሩ ግን በሃይማኖት ጸንተው ምግባር ትሩፋት ለመሥራት ቀና ደፋ ሲሉ ለነበሩ አማንያን በሞቱ ጊዜ ጸሎተ ፍትሐትና ተዝካር ታደርጋለች ። ለሟቹም ሆነ ለቋሚው የሚጠቅም መሆኑንም ታምናለች ።

በወንጌል እንዲህ የሚል ታሪክ ተዘግቧል ። አንድ የምኩራብ አለቃ ልጁ ታማበት ጌታችንን እንዲፈውሳት ሊለምነው ወደ ጌታ ዘንድ ይሔዳል ዳሩ ግን ልጅቱ መሞትዋን ሌሎች ያረዱታል ውጤት ለሌለው ነገር ጌታንም ማድከም አስፈላጊ አለመሆኑን ነገሩት ። ምንም



www.ethiopianorthodox.org

እንኳን መልእክተኞቹ ተስፋ ሊያስቆርጡት ይህን ቢናገሩም ጌታ ግን ለዘያ ሰው የተናገረው ቃል የሚያጽናና ነበር «እመን ብቻ እንጂ አትፍራ» የሚል ይህ አነጋገር ቀቢጸ ተስፋን እንደጢስ አትና እንደ ጉም አብና ከዚያ ሰው ህሊና ያጠፋ ነበር ። በእርግጥም ጌታ እንደተናገረው የሞተችይቱን ልጅ አስነስቷታል ። ማርቆስ ፭ ቁ. ፴፭—፴፮ ።

አዎን «የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እምነት ቢኖራችሁ...... የሚሳናችሁ ነገር የለም» ማቴ ፲፯ ቁ. ፲፱ መባሉን ከህሊናችን ሰሌዳ ላይ ልንፍቀው አይገባም በወንጌል የተጻፈው ሁሉ የዘመን ፍፃሜ የደረሰብንን እኛን ሊያስተምርና ሊገስጽ እንደተጻፈ ከማንኛውም የወንጌል አማኝ የተሰወረ ነገር አይደለም ። ታዲያ ከምኩራቡ አለቃ በዛሬ ዘመን ያለነው ክርስቲያኖች የተማርነው ትምህርት ምንድን ነው በእምነት ለሞቱ ወገኖቻችን ሞተ ነፍስ እንዳያገኛቸው ብንጸልይ ከወንጌል ውጭ ያሰኘናል በፍጹም ። እንዳውም በፍጹም ልባችን በጌታችን አምነንና ተማምነን በሙሉ ተስፋ መለመን እንዳለብን ጌታችን በዚህ ሰው አንጻር አስገንዝቦናል ።

ዛሬም ቢሆን እኮ እኛ ለሞቱ አማንያን ወገኖቻችን የምናደርገውን ጸሎተ ፍትሐት እንደማይጠቅምና እንደፈሰሰ ውኃ አድርገው የሚያቀርቡ ወገኖች አሉ እነዚህ ወገኖች ከላይ በማርቆስ ወንጌል እንደተጠቀሰው ሁሉ የምኩራቡን አለቃ ተስፋ ለማስቆረጥ እንደሞከሩት ሰዎች ሲመስሉ በክርስቶስ ላይ እምነት ያለው ክርስቲያን ግን ጌታ ለምኩራቡ አለቃ «እሙን ብቻ እንጂ አትፍራ» ያለውን አምላካዊ መልስ በልቡናው ጽላት ላይ ቀርጾ ተስፋ ባለመቁረጥ ቤተ ክርስቲያን ያዘዘችውን ማድረግ አለበት ። የምኩራቡ አለቃ ልጅ ከሥጋ ሞት እንደተነሳች ሁ ሉ ዛሬም በሕይወት ሥጋ ያለው ክርስቲያን ከዝች ምድር ላይ በሞት ለተለየው ክርስቲያናዊ ወገኑ ዘላለማዊ ሞት እንዳይገጥመው ቢጸልይለት ጌታ እንደ እምነቱ ያደርግለታል የሚል እምነት አለን ።

ተስፋ መቁረጥ የአሕዛብ እንጂ የክርስቶሳውያን አይደለም ክርስቲያን ባለ ተስፋ ነው «በተስፋ ደስ ይበላችሁ» ተብሎ እንደተጻፈ ሮሜ ፲፪. ቁ. ፲፪ ።

ይህን እንድናስተ ውል ይገባል ። ዛሬ በክርስቶስ ደም ተመሥርተናል ያልነው ሰዎች ጥንት ጌታ በሥጋ ይመላለስ በነበረበት ወቅት



ካሉት ሰዎች ያነሰ እምነት እንዳለን ። ምክንያቱም እነዚያ አምላክ ወልደ አምላክ በሥጋ መምጣቱን ሳያውቁ ዳሩ ግን በእምነት ብቻ የሞቱ ወገኖቻችውን እንኳን እንዲያድን እንደ ተማጸኑት ። በእምነት ያቀረቡት ልመና ግን መልሱ ልቡናን በትፍስሕት የሞላ እንደሆነ ወንጌልን ስናነብ የምናገኘው አማናዊ ነገር ነው ። ዛሬ ግን እኛ ከእነሱ ይልቅ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት አውቀን በስሙ አምነን ተጠምቀን እያለ ነገር ግን የአምላካችንን የማዳን ኃይል የምንጠራጠር አለን የአምልኮት መ ልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደውታል» የተባለው ለእንዚህ ከሀዲዎች ነው ። ስለዚህ የአምላካችንን የማዳን ኃይል በፍጹም ልባችን የምናምን ክርስቲያኖች በእምነት ለሞቱ ወገኖቻችን የምናቀርበው ፍትሐትና ጸሎት ተዝካር በአየር ላይ የሚቀር ሳይሆን በቅድመ እግዚአብሔር ደርሶ ግብ የሚመታ ነው ። በወንጌል ተከትቦ የምናነበው ሁሉ የሚያረጋግጠው ይህን ነውና በእምነት ወደ ክርስቶስ የቀረቡ ሁሉ ድህነተ ሥጋ እንዳገኙ ዛሬም ክርስቲያኖች በእምነት ወደ ጌታችን በመቅረብ የሞቱ ወገኖቻችን ድህነተ ነፍስ እንዲያገኙ ልናስደርግ እንችላለን «የምትሹትን ለምኑ ይሆንላችሁማል» ተብለናልና ለሚጠራጠር ሰው ግን ከጌታ ዘንድ አንዳች አይደረግለትም ። እምነታችን ነቅ የሌለበት ፍጹም እንዲሆን ተጽፏልና ።

«እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል» ዮሐንስ ወን ፲፬. ቁ. ፲፪ በዚህ አምላካዊ ቃል መሠረት ዛሬ ካህናት አባቶቻችን ለሞተው ምእመን የሚያቀርቡት ጸሎተ ፍትሐት ጠቀሜታ እንዳለው እንገነዘባለን ።

በኢዮጴ የተፈጸመው አማናዊ ድርጊት ለእዚህ እምነታችን ዓይነተኛ ምሥክር ነው ። «በኢዮጴጣቢታ የምትባል መልካም ደቀ መዝሙር ሞተች ደቀ መዛሙርቱ ጴጥሮስ በዚያ አካባቢ እንዳለ ሰምተው ወደ እነርሱ እንዲመጣ ለመኑት ጴጥሮስም መጥቶ ተንበርክኮ በመጸለይ ጣቢታ ሆይ ተነሺ ብሎ ከሞት አስነስቷታል ሥራ ፱. ቁ. ፴፮—፵፩ ።

እንደዘሁ ሁሉ እንደ ጣቢታ የሞተው ምእመን እንደ ደቀ መዛሙርቱ የሚች ወገኖች እንደ ጴጥሮስ ወደ ጌታ ለምኖ ጣቢታን ከሞት ሥጋ እንዳስነሳት ሁሉ ዛሬም አእይንተ እግዚአብሔር የተባሉ ካህናት ወደ ጌታ ጸልየው ከሞተ ነፍስ ያድኑታል ። ስንል እናምናለን »



www.ethiopianorthodox.org

ሎሞተው ምእመን ወደ ጌታ ጸልየው ከሞተ ነፍስ ያድኑታል ። ስንል እናምናለን» ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያን ቀሳውስት ወደ እርሱ ይጥራ በጌታም ሥም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል ኃጢአትንም ሠርቶ እንደሆነ ይሰርይለታል» ያዕ. ፭. ቁ. ፲፭ ።

ከዚህ እንደምንረዳው የእምነት ጸሎት ከኃጢአት ማሠሪያ እንደ ሚፈታ ነው ። ምንም እንኳን ሟች ራሱ ጦጦቶ ጸልዩልኝ ባይልም ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ሁሉ ብዙዎች ፈውሱን ያገኙት በወገኖቻቸው ልመናና ምልጃ መሆኑን ማስተዋል ይገባል ። ጌታም እምነታቸውን አይቶ እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ በማለት የፈለጉትን ፈጽሞላቸዋል ።

ሐዋርያት በሲኖዶስ እንዲህ ብለዋል «የሞቱ ዘመዶቻችሁን ኹል ጊዜ በቁርባን በቅዳሴ አስቧቸው ይህ እነሱን እጅግ ይጠቅማቸዋል ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር በባለሟልነት ያቀርባቸዋልና ።»

ርቱአነ ሃይማኖት 318 ሊቃውንትም በፍትሐ ነገሥት «ጌታ በሦስተኛው ቀን ስለተነሣ ስለሞቱ ሰዎች በመዝሙር በጸሎት በሣልስቱ መታሰቢያቸውን አድርጎ እንዲሁም የእስራኤል ልጆች በሞዓብ ሜዳ ሠላሳ ቀን ለሙሴ ያለቀሱለትን በማዘከር እናንተም በቀደሙቱ ሰዎች አምሳል ለሞቱ ወገኖቹ ቤተሰቦቻቸው በሠላሣቸው መታሰቢያቸውን አድርጉላቸዋል ።

ከሞተው ሰው ገንዘብ ለነዳያን ስጡ መታሰቢያ ይሆንለት ዘንድ በዚያን ቀን ብትጠሩ በሥርዓትና እግዚአብሔርን በመፍራት ብሉ።(49)

ከሰባ አርድእት አንዱ የሆነ ቀሌምንጦስ ወንጌልን በዓለም ዞሮ እንዳስተማረ ብርሃነ ዓለም ጳውሎስ በፊልጵ ፬. ቁ. ፫ ላይ መስክሮለታል ይህ ቀሎምንጦስ ለምውታን አማንያን ሊደረግ ስለሚገባው ነገር እንዲህ ይላል ።

---

49 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 22



«ለሞተ ሰው ከገንዘቡ ለነዳያን ይመጽውቱለት ቁርባን ያስቆርቡለት ዕጣን ያሳርጉለት ነፍስ ከሥጋዬ ከተለየሁ በኋላ ከቁርባን ከዕጣን ከመሥዋዕት በቀር ምንም የረባኝ የጠቀሙኝ ነገር የለም ዕረፍትም የለኝም መሥዋዕት በተሠዋልኝ ቁርባን በተቀረበልኝ ዕጣን በታጠነልኝ ጊዜ ግን ከዘመዶቹ ጋር ደስ ይለኛል ብላለችና ሙሽራው በሚጉላው ከዘመዶቹ ጋር እንዲደሰት ለነፍስም ዕጣን ካሳጠኑላት መሥዋዕት ከሠውላት ቁርባን ከአስቀረቡላት ከዘመዶቿ ጋር በሰማይ ተድላ ደስታዋ እንደዚህ ነው ።

ዘመዶቻችሁን ከወደዳአቸሁስ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጃት ዓይን ያላያት ጆሮ ያልሰማት መንግሥተ ሰማያን ይወርሱ ዘንድ ጸልዩላቸው ንጹሕ መሥዋዕት ሠውላቸው ቁርባን አስቁርቡላቸው ለነዳያንም መንፈሳዊ ምጽዋት መጽውቱላቸው ።

ለአባቶቻችሁ ለወንድሞቻችሁ ለልጆቻችሁ ለወገኖቻችሁ ተዝካር አውጥታችህ ላቸውፍታት አስፈትታችሁላቸው ይህን በማድረጋችሁ ከነሱ ጋር ደስ ይላችሁ ዘንድ ይህን አድርጉ ብዬ እነግራችኋለሁ እንደ አረማውያንና እንደ አሕዛብ ከሞቱ በኋላ ምን ይረባቸዋል ምን ይጠቅማቸዋል አትበሉ እንዲህም የሚሉ ሰዎች ትንሣኤ ሙታን እንዳለ የማያምኑ ተስፋ ትንሣኤ የሌላቸው ናቸው» (ቀሌምንጦስ ተመልከት)

አንድ ምእመን ሲሞት ወደ መቃብሩ በሚጓዝበት ጊዜ በሰባት ምዕራፍ ሰባት ጊዜ ጸሎተ ፍትሐት ማድረስ ይገባል ፡ ይኸውም ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወረሰ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥርዓት ነው እስራኤል የኢያሪኮን ከተማ ሰባት ጊዜ እየዞሩ በጸለዩ ጊዜ የብረት ቅጥሩ (አጥሩ) ፈራርሶ ወድቋል) መጽ. ኢያሱ ፮. ቁ. ፳ ።

የዘመነ ሐዲስ ካህናትም ጽንሐውን ይዘው እያጠኑ ቤተክርስቲያኑን ሰባት ጊዜ እየዞሩ ለእስራኤል የኢያሪኮን ቅጥር እንዳፈራረሰ ሁሉ ዛሬም የምእመናኑን ኃጢአት ደምስስልን በማለት ይጸልያሉ ለሞተውም ምእመን በዚሁ ምሳሌ ሰባት ጊዜ እየጸለዩ ቅጽረ ኃጢአቱን አፍርስለት (ማረው ይቅር በለው) እያሉ ጸሎተ ፍትሐቱን ያደርሱለታል ።



www.ethiopianorthodox.org

በተጨማሪም ነቢዩ ኤልሳዕ የሞተውን ሰው ሰባት ጊዜ ጸልዮ አስነስቶታል ። ነገሥት ካልዕ ፬. ቊ. ፴፫—፴፮ ። በዚያ ምሳሌ ዛሬም ለሞተው ሰው በሰባት ምዕራፍ ሰባት ጊዜ ጸሎተ ፍትሐት ይደርሳል ።

ዳግመኛም ልዩ ምሥጢር አለው ሰባት፣ሰው ሰባት ባሕርያት ያሉት መሆኑን ያመለክተናል ሰው ማለትም ከሰባት ነገሮች የተሠራ ማለት ነውና ። እነዚህም አራቱ ባሕርያተ ሥጋ እሳት ፣ መሬት ፣ ውሃ ፣ ነፋስ ሲሆኑ ሦስቱ ባሕርያት ነፍስ ደግሞ ለባዊነት (ልብማድረግ) ነባቢነት (መናገር) ህያውነት ናቸው ። በእነዚህ በሰባቱ ባሕርያት ተደፋፍሮ የፈጸመውን ኃጢአት ይቅር ብለህ ማርልን ብሎ መጸለይ ነው ።

እንዲሁም በዕብራውያን አቆጣጠር ሰባት ቁጥር ፍጹም ስለሆነ የሞተውን ምእመን መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ፍጹም አድርግልን ብሎ መለመን ነው ። 50

(50) መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ገጽ 44



www.ethiopianorthodox.org